# ምሥጢረ ጥምቀት

## የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀት

የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀት በብሉይ ኪዳን እንደነበሩት እንደ አይሁድና እንደ ዮሐንስ ያለ ጥምቀት አይደለም፡፡ ጥምቀተ አይሁድ ትዕዛዘ ኦሪትን ለጣሰ ሰው ይደረግ የነበረ የውኃ መታጠብ ነው፡፡ ከርኵሰት የሚነጻው በውኃ በመታጠብ ነበር (15÷1-18)፡፡ የዮሐንስ ጥምቀት ደግሞ የንስሐ ነበር (ማቴ.3÷5 እና 6)፡፡

ጌታ በዮሐንስ እጅ በባሕረ ዮርዳኖስ የተጠመቀው እንደ አይሁድ ሥርዓት ለመንጻት እንደ ዮሐንስም ጥምቀት ለሥርየተ ኃጢአት አልነበረም፡፡ ዳሩ ግን ስለሚከተሉት ምክንያቶች ተጠምቋል፡፡

### 1ኛ. ትሕትናን ለማስተማር

በአገልጋዩ (በፍጡሩ) በዮሐንስ እጅ መጠመቁ መምህረ ትሕትና መሆኑን ይገልጣል፡፡

### 2ኛ. ለእኛ አርአያ ለመሆን

ሁለተኛም በጥምቀት ዳግም ከእግዚአብሔር ለምንወለድ ለእኛ አርአያ ለመሆን ሊጠመቅ በቅቷል፡፡

### 3ኛ. ዲያብሎስ በዮርዳኖስ ወንዝ ደብቆት የነበረውን የዐዳ ደብዳቤ ለመደምሰስ፡፡

### 4ኛ. አንድነቱንና ሦስትነቱን ለማግለጥ

በብሉይ ኪዳን በተለያየ ኅብርና ምሳሌ የነበረውን አንድነቱንና ሦስትነቱን ለመግለጥ ጌታ ተጠምቋል፡፡ ‹‹ሰማያት ተከፈቱ›› የሚለው አነጋገር ሥውር የነበረው ይህ ምሥጢር መገለጡንና ገሃድ መውጣቱን የሚያስረዳ ነው፡፡ የተዘጋ ቤት ሲከፈት በውስጥ ያለው የተሠወረው እንደሚታይ ሁሉ ከሰው ከእምሮ ረቅቆ የነበረው የሥላሴ ምሥጢርም በጌታ ጥምቀት መገለጡን ያረጋግጣል፡፡ በዚህም ጊዜ የክርስቶስ እውነተኛ አምላክነት በባሕርይ አባቱና በባሕርይ ሕይወቱ በመንፈስ ቅዱስ ተመስሯል፡፡